# ***<u>የሠላማዊ ትግል ወይስ የትጥቅ ትግል "ትብትብ"</u>***

## ይድረስ ለእነ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ

## <u>እንደመነሻ</u>

ብዙውን ጊዜ ጹሁፎች ከተለያየ ፍላጎት ወይም ከጸሃፊው ሥነ ልቦናዊ ዝግጅት አኳኣያ ተረቀው ለንባብ የሚበቁ መሆናቸው አያከራክርም። በዚያው መጠን የፊና ወይም የቡድንን አቁኣም በመያዝ በተለይም በፓለቲካው ዓለም የተለያዩ ክርክሮች ይካሄዳሉ። በዚህ አመለካከቶችን ወይም አስተሳሰቦችን መቅረጽ ብሎም ወደ ገንቢ መስመር መሸጋገር ይቻል ይሆናል። በዚህ የግንዛቤ አቅጣጫ በመመርኮዝ በቅርቡ ምንም እንኳእ በአንደኛው ፀሃፊ ስም ጉዳዩ እየተነሳ መወያያ ቢሆንም በሁለት "በስም" በተመለከቱ ጸሃፊዎች በወጣ ጹሁፍ ዙሪያ ላይ የዚህ ጹሁፍ አቅራቢ የበኩሉን ሊል ይሻል። በቀዳሚነት ይህን አስተያየት የሚጋሩት ቢኖሩ እንኳእ የአጋጣሚ እንጂ የማንኛውም ግለሰብ ፤ ፊና ወይም ቡድን ወካይ እንዳልሆነ ለማስመር እወዳለሁ።

ለዚህ አስተያየት መነሻ ሰበብ የሆነው "ለወደፊቱ ትግል ማመላከቻ የምርጫ 97 አጭር ግምገማ" በሚል በእምነቱ ዘለቀ እና በአንዳርጋቸው ጽጌ "የተጻፈው " ነው። ይህን አስተያየት ለመስጠት ስነሳ ያሳሰበኝ በርግጥ የሁለት ሰዎች የጹሁፍ መዋጮ ይሁን አይሁን ማወቁ ሳይሆን መልሱ ወይም መከራከሪያ ሃሳቡ ምን መልክ ሊኖረው ይገባል? በሚለው ላይ ነው። ወዲህ ደግሞ በተለያዩ አጋጣሚዎች ጹሁፉ የአንዳርጋቸው ጽጌ የብቻ ተደርገው ሲነገሩ አደመጥን ፤ ራሳቸውም በዚህ ጹሁፍ ዙሪያ አስተያየታቸውን ሲያስደምጡን ይህንን አንድምታ አጠንክረዋልና ክርክሩና የሃሳብ ሙግቱ ወደርሳቸው እንዲያዘነብል እያደረገው መሆኑም ግልጽ ነው ማለት ስህተት አይሆንም። እንደእርሳቸው አንደኛው ፀሃፊም በእምነቱ ዘለቀ (የፈረስ ስም ካልሆነ) ቀርበው ሃሳባቸውን ባያብራሩም አንዳርጋቸው በሚገባ ሸፍነውታልና ወደዚያ አዘንብሎ መነጋገሩ ጠቀሜታ አለው ብሎ ይሄ ፀሃፊ ያምናል።

እንደገናም መልሱ አሁን ወይስ ይቆይ በሚለው ላይ ደጋግሜ ከራሴ ጋር መከሬአለሁ ። ተከታይ ጹሁፍ እንዳለ ተመልክቱአልና ያንን መጠበቅ የሚልም ፍላጎት ሳያድርብኝም አልቀረም። ይሁንና ተመሳሳይ ባህርይ ሊኖረው ይችላል በሚል አሁኑኑ መጻፉ ጥሩ ይሆናል የሚለው ስሜቴ አሸንፎ አሁን ላቀርበው መረጥኩ ። ከተነሱት ነጥቦች ስፋት አኳኣያ ትንሽ ረዘም ማለቱ ቢገባኝም ለረጅም ትግል የተነሳ መንፈስ ይህን ለማንበብ አይሰንፍም በሚል እንዳለ ላቀርበው መርጫለሁ። መልሱን አሁን እንደሰጥ ያደረገኝ ሌላ ምክንያት መኖሩንም ሳልጠቅስ ማለፍ አልችልም። እውነት ሆኖ መሳሪያ ከተነሳ በሁኣላ ከሆነ ግን እንዳልፈራ ብዬ ለራሴ ሰጋሁ። አጥብቄ የምደግፈው ሰላማዊ ትግል "የፈሪዎች"ምርጫ ነውና።

ከዚህ በተጨማሪ ይህን መሰል በፓለቲካ ጉዳይ የቀረቡ የመወያያ ነጥቦችን በተለይም የትግል ስልትን አስመልክቶ የሚቀርቡ የውይይት ሃሳቦችን ከጸሃፊው ለይቶ በሃሳቡ ላይ መሙኣገቱ በተለይም ፀሃፊውን የማያውቁት ከሆነ ሰናይ ነው ። ይህ ባይሆን እንኳእ ፀሃፊውን ቢያውቁትም በተቻለ መጠን ሁለቱን ለመለየት መጣሩም ተገቢነት አያጣም ። እዚህ ላይ ግን ይህን ለማድረግ ለሚጥር ሰው አስቸጋሪ የሚሆነው ፀሃፊው አንዳርጋቸው ጽጌ ያላቸው የፓለቲካ ጀርባ ወይም የሁኣላ ታሪክ እየመጣ ስንቅር የማለቱ ብቻ አይደለም ። ይልቁንም እርሳቸው ይህን አዲስ የወጡትን የትግል ስልት

በአጋፉሪነት ሊሳተፉበት ቀርጠዋልና (በእርሳቸው ገለጻ መሰረት) በጹሁፉ የቀረበውን መከራከሪያ ከነእርሳቸው ለይተን ከማየት አጣምረን ማየቱ ጠቀሜታው እንደሚጎላ ግልጽ ይሆናል። ትግሉ ከሚጠይቀው ዋጋና ጽናት አኩአያ ቢያንስ ቢያንስ አብሮ ለመሰለፍ በሚያስችል ሥነ ልቦናዊ ዝግጅትና መተማመን ላይ ለመመስረት ጥርጊያ ይሆናልና።

ወደ ርዕሰ ጉዳዩ ከመግባቴ በፊት አንድ ነጥብ ላክል፤ በተለይም በሃገራችን ስላለው ፖለቲካዊ ተሳትፎና ውጤቱ። ደጋግመን እንዳየነው በሃገራችን ሕዝብን ለማስተዳደር በሚል የሚነሳ ፖለቲካዊ ንግግር ጦርነት ፤ በብዙዎችም ዘንድም አይነኬና ተፈሪ ሆኑኣል። ጦርነት የመሆኑ ጉዳይ ደጋግመን በደም ዋጋ የሚጨበጥ እንጂ ስልጡን አካሄድን ሊያሳየን ባለመቻሉ ነው፤ አይነኬነቱ ደግሞ በሚያደርሰው እንግልትና ጫና የአብዛኛውን ሕዝብ ሥነ ልቦና በፍርሃት ድባብ እንዲዋጥ በማድረጉ ነው። ዛሬ ሊያነጋግረን ብሎም የመፍትሄ ሃሳብ እንድናፈልቅ ግድ የሚለን ይህ የምንገኝበት አዙሪት ሙሉ በሙሉ ጥፋታችንን ሳያውጅብን ቀድመን መገኘት ስለሚያሻን መሆኑ አያከራክርም።

ለዚህ ደግሞ የምንመርጠው የመፍትሄ መንገድ ቀዳሚውና ወሳኙ ነው። ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት የምናሳየው መነሳሳት የጉዞአችንም ጥርጊያ ይሆናል። በሙአቶች ብዛት፤ በዜጎች መታሰር ፤ መደብደብ ወዘተ የትግል ጉዞአችንን መለካቱን ልናቆምም ይገባናል። የአንድ ሰው ህይወት መጥፋት ቀርቶ በጥፊ መመታት ለምን? የሚል መቆጨትና የጋራ ግንዛቤ መፍጠርም ያሻናል።

“ዶሮ ብታልም...” እንዲሉ አምባገነን አገዛዞች የህዝብ የተቃውሞ ስሜት ያስደነብራቸዋል ። የመጡበት መንገድና የያዙት ደልዳላ የመሰለ የሚሞቅ ወንበር ያነሆልላቸዋል። ደንብረው ይራገጣሉ፤ በግድያ ዛር ተንዘፍዝፈው ሰብዓዊ ህሊና የማያደርገውን አረመኔአዊ ድርጊት ይፈጽማሉ። ወያኔ በዚህ ረገድ የተካነ ነውና ስለርሱ ባህርያት እያነሳን ለማስረዳት በመሞከር መድከም አይኖርብንም። ዞረን ዞረን ወደ መፍትሄው ጥርጊያ ስንመጣ የምንመርጠው መንገድም ይሁን ስልት መመዘን ያለበት ከውጤቱና ከዋጋው አኩአያ ሊሆን ይችላል። ለበደል መፍትሄ ለመሻት ስንነሳ ሌላ በደልን ወይም ቂምን ላለማፍራት ምን ያህል ፀንተናል? ያየናቸው ሥረዓቶች ምን ዘርተው ምን አጨዱ? የወያኔ መሪዎች ተበደለ ብለው ነፍጥ “ላነሱለት” ሕዝብ ምን ፈየዱ? በደሉን አጸዱለት ወይስ ጨመሩበት? ይህ እንደየቆምንበት መሬት የሚመዘን ቢሆንም ኢትዮጵያና ሕዝቡአ ዛሬ ያሉበት የአዘቅት ጎዳና መሆኑ ላይ ልዩነት የሚኖረን አይመስለኝም።

እንዲደረግ ከምንፈልገው ወይም ይብዛም ይነስ እንደ አቅምቲ በምንደከምበት የፖለቲካ ተሳትፎና ትግል የምንፈልገው አብይ ቁምነገር አንዱ የሥርዓት ለውጥ ነው። ይህ የሥርዓት ለውጥም ሥልጣን ከሕዝብ ይሁንታ የሚመነጭ መሆኑን የሚያረጋግጥ መሆኑን ዋስትና የሚሰጥ እንዲሆንም ነው ጥረቱ። በዚህ መንገድ የተረጋገጠ ሥልጣን በሚያደርገው የዴሞክራሲ ሥርዓት ምስረታ ሂደት ራሱን ብቃት ወዳለው የሕዘብ አስተዳደር ያሸጋግራል ማለት ነው ። ከዚህ በተጉአዳኝ ከሚደረገው ፖለቲካዊ ተሳትፎ የምንሻው ሌላው ቁም ነገር በዜጎች ዘንድ ጠንካራ ብሔራዊ ስሜትን የመገንባት ይሆናል። ይህ በተለያየ ርዕዮት የተሰለፉ የፖለቲካ ኃይሎችም ቢሆኑ በሚያገኙት የተሳትፎ የእኩልነት ሜዳ ይህን ጥያቄ የመመለስ (የሚቆሙለት ዓላማ ነውና ) ዕድል ይገጥማቸዋል።

ወደ ሥልጣን ጥያቄ ሲመጣ ከፖለቲካ ኃይላቱ ውስጥ ምን ያህሉ ከጠባብ ቡድናዊና የንዋይ ፍትወት ባሻገር ሥልጣንን ያልማሉ? ምንስ ያህሉ አጋጣሚውን ሃገርንና ሕዝብን ለማገልገል ብሎም

ለማሳደግ ይወጥናሉ ? የሚሉትም በሂደቱ የሚመዘኑ ጉዳዮች ናቸው። ምናልባት ለመጀመሪያው ጥያቄ ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ አያሻው ይሆናል። ገዳይነትን ፤ ጭካኔን ፤ ይሉኝታ ቢስነትን ፤ ቡድንኝነትንና ከፋፋይነትን መካን በቂ ነው። ለሁለተኛው ጥያቄ ግን ጤናማ የሃገር ፤ የወገን ፍቅርን አጥብቆ ይሻል። ከግል ዝናና ፍላጎት ተሻግሮ የሚያልም ፤ በጎ ተመኝቶ አወንታዊ አስተጽዎ ለማድረግ መነሳሳትን ያጠይቃል። ይህ ርእሰ ጉዳይ ራሱን ችሎ ብዙ የሚያወያይ ቢሆንም ለተነሳንበት ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ በላይ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ መግባቱ ላይጠቅም ይችላል። የሃይል የትግል ስልትን እንደ አማራጭ ይዞ ብቅ ያለውን የአንዳርጋቸው ጽጌን ጹሁፍ ለማየት የምሞክረው ከላይ የተነሱ አንኩአር ነጥቦችን ታሳቢ በማድረግ ይሆናል።

## ***<u>በጹሁፉ ላይ ፦</u>***

“ለወደፊቱ ትግል ማመላከቻ የምርጫ 97 አጭር ግምገማ ” በሚል የወጣው ጹሁፍ ርዕሱ እንደሚያመለክተው ግምጋሜው በርግጥም አጭር ነው። ይህን ትልቅ ዋጋ ለሚጠይቅ የትግል ስልት የቀረበ አማራጭን በአጭር ግምገማ ለምን እንዳቀረቡ ፀሃፊው ቢያውቁትም እኛ ተራ አንባቢዎቹ ከጥርጣሬና ከግምት ያለፈ መረጃ ላይኖረን ይችላል። ቢሆንም ግን ፀሃፊው በግንቦቱ ምርጫ በቅንጅቱ ተሳትፎና ውጤቱ የሰላማዊ ትግል ትዕግስታቸው ተሙአጦ ማለቁን አልሸሸጉም ። አጭር እይታ በምን አይነት መንገድ ዘለቄታ ላለው ሂደት እልባት ለማበጀት እንደሚረዳም ወደፊት እንደሚያስረዱን ተስፋ በማድረግ እንለፈው። በተጨማሪም ጹሁፉን በተሙአጠጠው የሰላማዊ ትግል ስሜታቸው ድምዳሜ አንባብያን አጋር እንዲሆኑ ደጋግመው ወትውተዋል። እስኪ ወደ ውስጥ ዘልቀን እንመልከት።

ለመነሻ ግን ፀሃፊው ደጋግመው የድምዳሜአቸው አጋር አንድንሆን እየገፉን ከመሄድ ፈንታ አሳማኝ ያሉትን መከራከሪያቸውን ሰንዝረው መጨረሻ ላይ የውሳኔአቸው ተጋሪ አንድንሆን የሚያደርግ አቀራረብን ቢመርጡ ኖሮ ጥሩ ነበር እላለሁ። ዳሩ ፀሃፊዎቹ ካላቸው ምሉዕ በኩሌህነት አኩአያ (ወደ ሁአላ ይብራራል) ይህ የሚጠፋቸው ባለመሆኑና ይሁነኝ ተብሎ የተመረጠ አቀራረብ በመሆኑ በአጉል መካሪነቴ ከወዲሁ ይቅርታ ልጠይቅ እወዳለሁ። ሌላው በጹሁፉ የሚስተዋለው አብይ ጉዳይ የቀረቡት መረጃዎች ባለፉት “ ጥቂት” ጊዜያት በአንደኛው በተለይም “ለዴሞክራሲያዊነት” ቆሜአለሁ እያለ በተደጋጋሚ ሲያውጅ በነበረው ፊና በኩል ሲቀነቀኑ የነበሩ ኩነቶች እንደሆኑ መገመተም አያዳግትም። ምናልባትም ይህ መንገድ የተመረጠው ወደ ሁአላ በመመለስ አንዳንድ እውነታዎችን ለመዳሰስ ከተሞከረ አንጥረው የሚመልሱአቸው ያልተጠበቁ ድንገቴዎች እንዳይኖሩ በመስጋት ሊሆን ይችላል በሚል ስስ ግምት እንለፈው።

ምናልባትም በጸሃፊው ግምት በዘመነ ወያኔ የተደረገው ሰላማዊ ትግል በግንቦቱ ምርጫ ዝግጅት ተጀምሮ በውጤቱ መሰረቅ ያበቃለት ተደርጎ ተወስዶ ሊሆን ይችላል።በጹህፋቸውም ላይ ስለቀደመው የትግል ጉዞና ውጤቱ አስመልክቶ ያሉት ባለመኖሩ በዚሁ በተነሳው ጉዳይ ላይ ብቻ ማተኮሩ ይሻላል።

“ ከምርጫ 97 ቀደም ብሎ በቴሌቪዥን መስኮቶች በተቃዋሚዎችና በወያኔ ኃይሎች መሃል ይደረጉ በነበሩ ክርክሮች ወቅት በተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች በኩል ይሰጡ የነበሩ አስተያየቶችን ለተመለከተ የዚህ አይነቱ የሕዝብ አቁአም የሚገርም አይሆንም፤” ብለዋል። ትንሽ ዝቅ በሎ ደግሞ፤ “በምርጫ 97 ዙሪያ የተነሳው እንቅስቃሴ የምርጫውን ውጤት አሰርቆ ለጊዜው ሊታፈን ችሉአል፤” የሚልም ይገኛል። ሁለቱም ገለጻዎች በቀጥታ ከላይ የተሰነዘረውን አስተያየት የሚያረጋግጡ አስረጂዎች

ናቸው። በተደረገልን ገለጻ መሰረት ሕዝቡ በግንቦቱ ምርጫ ያሳየው ተሳትፎ በዚያ “በቴሌቪዥን መስኮት” በቀረበ የሁለትና የሶስት ወር ቅስቀሳ ነው። ሌላው ቀርቶ ቅንጅቱ ድል ያደረገባቸውን አካባቢዎች የቴሌቪዥን ሥርጭትን አቅርቦትና ምን ያህሉስ ያንን ቀርቶ የሬዲዮ ማድመጥ ዕድል እንደነበረው ሳንዘነጋ ። የኅብረቱን ደግሞ እዚህ ላይ እንጨምረውና እንመልከተው። ይህ በዚህ በአቶ አንዳርጋቸው ጹሁፋ ተደጋግሞ የቀረበ በመሆኑና ምንን ሊያስተላልፉ እንደፈለጉ ፍንትው ብሎ ስለሚታይ ወደ ሁኣላ እመለስበታለሁ።

ወደ አዲሱ የትግል ስልት መንደርደሪያ ስናመራ ጠቅለል ባሉ ጉዳዮች ላይ አስተያየቴን ለመሰንዘር እሞክራለሁ። በጀኦ ፓለቲካዊ ስሌቶች ዙሪያ አንደታሪካዊ ዳራ በቀረቡት ጥቅል አስተያየቶች ላይ ብዙም መከራከር አያሻ ይሆናል ፤ በተለይም በምዕራባውያን አይታ ዙሪያ። ከዚህ በተጉአዳኝ ግን የወያነ ባለስልጣናት በምርጫው ላይ ስለነበራቸው አይታ አስመልክቶ በቀረበው ላይ ጎደሎነት ይታያል። ፀሃፊዎቹ ለሚፈልጉት የድምዳሜ መደረሻ ይረዳል በሚል ካቀረቡት በተጨማሪ  በገሃድ ይታዩ የነበሩ እውነቶች አሉ። እነዚህን ጉዳዮች ፀሃፊዎቹ አካተዋቸው ቢሆን ኖሮ ምናልባት ከላይ ግምጋሚው አጭር ነው በሚል የቀረበውን አስተያየት በመጠኑም ቢሆን ያለዝበው ይችል እንደነበር አምናለሁ።

እነዚህን ነጥቦች ላነሳ የምሻው በስሚ ስሚ ሳይሆን እስከመጨረሻዋ ዕለትና እስካሁንም ድረስ በውስጡ አለሁበትና ከማውቀው እውነት በመነሳት መሆኑን ማሳወቅ አወዳለሁ። በተለይም ደግሞ ቅንጅቱም ሆነ ኅብረቱ ድልን ባገኙባቸው የሃገሪቱ ክፍሎች ከቅንጅቱ ምስረታ ዓመታት ቀደም ብሎ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚያስደፍር እንቅስቃሴ መሳተፍ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማነጋገር በቂ ግንዛቤ አለኝ ብዬ ስለማምን ነው ቢካተቱበት አይታውን ያሰፉዋል የሚል ግዛቤ ያደረብኝ።

ከነዚህ መሃል አብይ ነጥቦቹ የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

- የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናትና ግልገል ሹማምንቶቻቸው ሕዝብ ይወደናል የሚለው ተአብዮአቸው። ደጋግመው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሲናገሩ ራሳቸውን እያደመጡ እንደ እውነት እየቆጠሩት መሄድ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎች አንድ የቦይ ድልድይ ሳይሰሩ እንዴት ለውድድር ይቀርባሉ? ወደሚል ተራ ግንዛቤና የአደባባይ ቅስቀሳ መውረዳቸው፤
- በስልጣን ፍትወት ሰክረው ተወዳዳሪ ፓርቲነታቸውንና መንግስትነታቸውን መዘንጋት ብቻ ሳይሆን ማስተዋል የሚባለውን ከሥነ ልቦናቸው ማጥፋታቸው፤
- መራጩን ሕዝብ በገንዘብ እንገዛዋለን ብለው መነሳታቸው፤ (በዚህ ረገድ ሕዝቡን በድህነቱ አፊዘው የበተኑትን ገንዘብ ያጤኑአል። እስታውሳለሁ አፋርና ምስራቅ ጎጃም ውስጥ በአንድ መንደር ውስጥ በተደረጉ ስብሰባዎች ላይ ነዋሪዎቹ ‘ መንግስት ገንዘብ ልስጣችሁ ይለናል ምን እናድርግ?’ ብለው ጠይቀው ነበር ። በወቅቱ ስብሰባውን ይመሩ ከነበሩት የቅንጅቱ ተወካዮች የተሰጣቸው መልስ  ‘ብልጥ ሁኑ ገንዘቡማ የናንተው ስለሆነ ተቀበሉ፤ የምተምርጡትን ታውቃላችሁ የሚል እንደነበር አልዘንጋውም፤ እዎ ወያነ ሁለቱን አጣ፤ ገንዘቡንም ድምጹንም። ለሚያዚያው ሰልፍም በቀን ሃምሳ ብር ውሎ አበል ከፍሎ አስወጣ፤ ያ ወጣት በማግስቱ ‘ትላንትና ለቲሸርት ዛሬ ለነጻነት’ ብሎ ቆመ እንጂ አልተገዛም።  በርካታ ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል።)

- መሬትን የፖለቲካ መጠቀሚያ ማድረጉ፣ እዚህ ላይ በግልጽ የወያነን የተሳከረ የመንግስትነትና የተወዳዳሪ ፓርቲነት ቀውስ መመልከት ይቻላል። በዚህ ተግባርም የተቃዋሚ አባል፣ ደጋፊ የሆኑ መሬትና ቤታቸውን ተነጥቀዋል። የማዳበሪያ አቅርቦትን በሞኖፖል የያዙት የህወሃት የንግድ ድርጅቶችን በመጠቀም የተቃዋሚ አባል የሆኑትን (በህግ የተሰጣቸውን መብት ተጠቅመው ማለት ነው) ዜጎች የመኖሪያ ቤት ከዳን ቀርቀሮ ሳይቀር ነቅለው ወስደዋል ፤ ከብቶቻቸውን ነድተዋል ወዘተ
- ጠንካራ የተባሉ አደራጆችን ከስራ ማባረር ፤ ማዋከብ ፤ መደብደብ ፤ ማሰር ፤ ወንዶችን ሚስቶቻቸው ፊት ብልታቸውን በመቀጥቀጥ መካን ማድረግ ወዘተ ከግድያ ጋር መፈጸም፣
- በሰላማዊ ትግል በቀዳሚነት ልሳንና አጋር ሆኖ ያገለገለው ያልተዜመለት የነጻው ፕሬስ ጽናት፣

ከነዚህም ባሻገር ብዙ ብዙ ጉዳዮችን መዘርዘር ይቻላል። ለዚህም ነው የግንቦቱ ምርጫ የሁለትና የሶስት ወር ግርግርና የቴሌቪዥን መስኮት ዲስኩር የወለደው አይደለም ሊባል የሚገባው።

ዛሬ ዋጋው እንሶ እንዲታይ የሚፈለገው ሰላማዊ ትግልና የታፈነው የሕዝብ ምሬት ጭምር እንጂ። ምናልባት አቶ አንዳርጋቸው በጹሁፋቸው አንዳንድ ቃላቶችን ሲጠቀሙ ለአሉታ ሳይሆን እንደ “የተለምዶ መድበል” ይታይልን ስላሉ እኔም በአንዳንድ ቦታ መሰል አገላለጾችን ባስገባ ለዘለፋ ሳይሆን በትክክል ይገልጸው ይሆን ብሎ ከመጨነቅ እንደተሰነዘረ “የተለምዶ” ቃል ይያዝልኝ።

ይህ ሁሉ ፈተናና እንግልት ሳይበግራቸው እነዚህ ዜጎች ለግንቦቱ ምርጫ ስምረት የደከሙ ናቸው ። ያልተዜመላቸው ፤ እንደዘመኑ ታንቲረኞች የአበባ ጉንጉን ባንገታቸው ያልጠለቀ የሰላማዊ ትግሉ ጀግኖችና አርዓያዎች ናቸው። በሞትና በስቃይ ፅናት ሌላውን ለማስተማራቸው ብዙ ህያው ምስክሮች አሉን። የነርሱ አሴት እንዲሁ መና ሊቀር አይገባውም። የነርሱ ፅናትም ነው በአብዛኛው የምዕራባውያንን ዕይታ የቀየረው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

አንድ አስረጂ ላቅርብ። ጊዜው ከቅንጅት ምስረታ ትንሽ ቀደም ይላል። በርግጠኝነት (እንደኛውን ጸሃፊ አላውቃቸውምና) ባያስታውሱት አቶ አንዳርጋቸው ዜናውን አይዘነጉትም ብዬ ብገምት ላልሳሳት እችላለሁ ። ናቄ አሰፋ ይባላሉ የቅንጅቱ አንድ አባል የሆነው የመኢአድ አባል ናቸው።(መኢአድ ማለቴ ጊዜው ከቅንጅት ምስረታ በፊት በመሆኑ ነው) ነዋሪነታቸው በምስራቅ ጎጃም የሆነ ታታሪ ገበሬ ናቸው። የፖለቲካ አመለካከታቸው ወንጀል ሆኖ ከሌሎች ወገኖቻቸው ጋር ለእስር ተዳረጉ ፤ተሰቃዩ ። አንዱን ቀን ግን ወሰኑ ። ከታሰሩበት እስር ቤት ቀርቀሮ ቀደው አመለጡ። ነገሩን ለማሳጠር አብዛኛውን መንገድ በግር ተጉዘው አባይን ተሻግረው በቀናት ውስጥ አዲስ አበባ ጎጃም በረንዳ ደረሱ። አጠያይቀው ድርጅቱ ጽ/ቤት ይሄዳሉ፣ የደረሰባቸውን የጉዳት መጠንና ያለውን ሁኔታ በሙሉ ያስረዳሉ። የነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞችና የኢሰመጉ ሰራተኞች በወቅቱ ስለደረሰባቸው የስቃይና የእንግልት መጠን እንደዚሁም እዚያ ሰለሚደረገው ኢ ሰብዓዊ ድርጊት በዝርዝር ዘግበዋል።

በጥቂቱ ለመግለጽ ያህል የአካባቢው የወያነ ባልስልጣናት ላስቲክ አያቀለጡ ሰውነታቸውን በሙሉ የቻሉትን ያህል ጠባብሰዋቸዋል። በወቅቱ ከ87 በላይ ቁስሎችን በመላ አካላታቸው ላይ ይታይ እንደነበር አስታውሳለሁ ። ናቄ አሰፋና ሌሎች ታሳሪዎች ታጉረው የተሰቃዩት ለማዳበሪያ ማከማቻ በተዘጋጀ የቀርቀሮ መጋዘን ውስጥ ነበር። ባለኝ መረጃ መሰረት በወቅቱ የድርጀቱ መሪዎች እንደ ሁልጊዜው ሁሉ ብዙም በወያነ ላይ ልባቸው ላልቀረጠው ለምዕራባውያን ዲፕሎማቶች በአካል ጨምር

ወስደው መረጃውን ያስዩአቸዋል። አሁንም በአጭሩ ለመግለጽ የአሜሪካና የእንግሊዝ ዲፕሎማቶች በዋንኛነት ያሉበት ካልተሳሳትኩ የአውሮፓ ተወካዮች የተሳተፉበት ቡድን ቦታው ድረስ ሄዶ ሊያጣራ ይወስናል ኖቄን ይዞ። ሚስጢራዊው ጉዞ ተዘጋጀ።

ለዚህ የምዕራባውያን ውሳኔ ምስጋና ማቅረብ ቢገባ ለማን እንደሚሆን መናገር ላያሻ ይችላል። መረዎቹ የቀሙለት ዓላማ ነውና። ይህን ማለቴ ዛሬ በምድረበዳ በተገኘ እድል በማያውቁት ሜዳ አጋፋሪ የሆኑትና በሞላ በጎደለው ሲንቀለጳጰሱ የሚውሉት አድርገውት ቢሆን ኖሮ የሚባለውን በመገመት ብቻ ነው። ድሪ ገጹ ተጣቦ ፤ ቅጥስ ብጥሱ ጉድ ነበር። ትራፊክ ፓሊስ መንገድ ላይ ጠየቀን ተብሎ የተወራውን አናስታውሰው የለ።ወደ ጉዳዩ ልመለስ።

ዲፕሎማቶቹ በውሳኔአቸው መሰረት አንድ ከፍተኛ የድርጅቱን የአመራር አባል በአስረጂነት ይዘው ኖቄን ጨምረው ማልደው አባይን ተሻግረው ደጀን ገቡ ። ያ የአባይን በረሃ በግሩ ያቋአረጠ ታሳሪ በዲፕሎማቶች መኪና ታጅቦ መንደሩን ረገጠ። የተባለውን የቀርቀሮ እስር ቤት ከውጭ የትኛው እንደሆነ ከተመለከቱ በሁአላ በቀጥታ የአካባቢውን ባለስልጣናት ሊያነጋግሩ ወደ ቢሮአቸው አቀኑ። ፈርንጆቹ ለበጎ አድራጎት ስራ የመጡ የመሰሉአቸው የአካባቢው ባለስልጣናት የሰበካ ድርድራቸውን አሰሙ። ትንሽ ለጥቀ ጥያቄው መጣ እንጂ። በቀጥታ ዜጎችን አስረው ለማሰቃየት ስልጣን ማን እንደሰጣቸው ጥያቄ አቀረቡላቸው። መልሳቸውም “ ፈጽሞ የማይደረግ ” የሚል ነበር።

ጊዜ ማጥፋት አልፈለጉምና ከዲፕሎማቶቹ አንዱ ወደ ሁአላ ዞር በሎ ሾፌሩን አነጋገሩ። ትንሽ ቆይቶ ከሾፌሩ ጋር አዲስ ሙሉ ልብስ የለበሰ ሰው መጣ። ባለስልጣናቱ ድንጋጤአቸውን መቆጣጠር አልቻሉም። ነገሩ እንደ ተበላሸ አወቁት። ሞተ ብለው ከነመኖሩም የዘነጉት ኖቄ አሰፋ ነበር። የሚገርመው ፈርንጆቹ ከውጭ ጉዳይ መ/ቤት በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል የመንቀሳቀስና የመጠየቅ መብታቸውን አስመልክቶ የተሰጣቸን ደብዳቤ አሳይተው በቀጥታ የተዘጋውን መጋዘን አስከፈቱ። አዎ! በዚያ ለነበሩት አትዮጵያውያን የፈጣሪ መልዕክተኛ የመጣ ነበር የመሰላቸው ። ከዚያ በሁአላ ወያኔ በአካባቢው ምን አደረገ? የሚለው ሌላ ታሪክ ነውና ልለፈው።

ዲፕሎማቶቹ ባገኙት መረጃ አላመኑቱም ፤ በአገዛዙ ላይ ያወጡትን መግለጫ ያጤኑአል። ትግሉ ብዙ ኖቄዎችን እያፈራ ቀጠለ። እነዚህ የሰላማዊ ትግሉ ቀንዲሎች ፤ በድጋሚ ለመግለጽ ያልተዜመላቸው ፤ መጽሃፍ ያልተደረሰላቸው ፤ በሞታቸው ብርሃንን ያስገኙ ብርሃናቸው የጨለመባቸው ኩሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው ። ጎህ ያልቀደደላቸው የሰላሙ ትግል ፍሬዎች ። እንግዲህ ይህን እውነት የመዘንጋት፤ ታሪክን የመሻማት አዝማሚያው ነው እጅጉን ልብ የሚያደማው። ክፍሉ ታደሰ በጻፉት የምርጫ 97 ግምጋሜአቸው ፤ ዶ/ር ብርሃኑም “ከወህኒ ባወጡልን” ጎህ ሲቀድ ድርሰታቸውም ይሁን አቶ አንዳርጋቸው ደጋግመው በሚያስነቡብን የቀስተደመና የአንበሳ ድርሻ ገድለታሪክ ትረካም የሚቀርብልን ሁሉ አዝማሚያው ይገባናል። በቅርቡ ደግሞ ምንም እንኳአ በልጅነታቸው ከሁለት መስመር ስንኝ ሌላ ጽፌ አላቅም ሲሉ የነበሩት ቲያትረኛው ደበበ “የጻፉት” ሳይጨመር ማለት ነው።( በነገራችን ላይ ዶ/ር ያዕቀብ ሃ/ማርያም ያወጡታል የሚባለው መጽሃፍ ሲወጣ ቀስተዳመና በመጽሃፍ አንበሽበሸን ማለት ነው። ፓርቲው በትግሉ ወስጥ አንድ ዓመት ከቆየማ በቃ ጉድ ነው።) በዚያው መጠን እውነታውን ሊናገሩ ፤ ፅፈው ሊያስነብቡን የሚችሉ የተባ ብዕር እንዳላቸው የምናውቃቸው ሰዎች ዝምታ በእጅጉ ከሚያስቀጫቸው ወገኖች አንዱ መሆኔን እግረ ነገሬን ጠቅሼ ማለፍ ተገቢ ነው።

እዚህ ላይ ምናልባት ከዚህ መሰል ስህተት የሚዶለው ቡድነኝነትና ስለራስ የሚኖር የተዛባ ግምት ሊሆን ይችላል። ከጹሁፉ አባባል ልዋስ። “ መለስ ዜናዊ እንደአሻንጉሊት ከሚጫወትበት ገደብ የለሽ ስለራሱና ስለማንነቱ ከነበረው የተጋነነ ግንዛቤ ጋር የተቆራኘ ነበር ፤ … የኢሕአዴግ ደናቁርት መለስ ዜናዊን እንደምድራዊ አምላካቸው አድርገው የወሰዱበት ሁኔታ ተስተውሉአል። ” ይህም ሁኔታ በዚህ አዲስ የትግል ስልት አቅራቢ ዘንድ የተስተዋለ ይመስላል።”የቅንጅት ስትራቴጂስት” ቅብጥርሶ እያሉ ስትራቴጂውንም ባናይም የሚፈጥረው ሙቀት ከባድ ነው።(ባደራጁት የፓልቶክ አንድ አጋፋሪም የቅንጅቱ ማኒፌስቶ ጸሃፊ ተደርገው ሲነሱ ሰምቻለሁና ሲደጋገም እውነት ይመስልና ሙቀቱ ቀላል አይደለም)። እንዲህ አይነቱም ሁኔታ የሚፈጥረው ሙቀት ፀሃፊውን ከመነሻው ላይ የተመለከተውን “ሙሉ በኩሌህነት ”የተላበሱ የአዳም ፍጡር ነኝ ብለው እንዲአስቡ ሳያደርግ አልቀረም።

እስኪ ከላይ የተመለከቱትን ጉዳዮች በጹህፉ ከቀረቡ መከራከሪያዎች ጋር እያዛመድን መመልከቱን እንቀጥል። በተለይም ደግሞ የተቃዋሚ ድርጅቶችን አሰላለፍ በቃኙበት ምዕራፍ ውስጥ የቡድነኝነት ስሜቱ ገንኖ ሲወጣ ይስተዋላል። ኅብረትን በተመለከተ ከአባልነት የወጡ ሁለቱን ድርጅቶች ለመንቀፍ በሚመስል የገደምዳሜ አነጋገር “ ከአግባቡ በላይ የሆነ ተጽእኖ ለማሳደር በመሞከራቸውና በአንዳንድ ድርጅቶች መሪዎች የገጸ ባህርይ አለመጣጣም ተቋአረጠ ” ይላሉ። ትንሽ ወረድ ብሎ “ መኢአድና ኢዴፓ የበለጠ ደጋፊ ሊኖራቸው እንደሚችል የሚገመቱ” የሚልም ሃረግ ሰፍሩአል።

ምናልባት ከኅብረት ጋር በተያያዘ ደፈር ያለ የግምጋሜ አስተያየት ከመስጠት የተቆጠቡበት ምክንያት ስላልነገሩን አናውቅም። የሚመጣውን የአፀፋ መልስ በመፍራት እንደሆነ ግን መገመት ምንም ስህተት አይደለም። ይህን ለመሰለ ትግል የቀረጡ ስትራቴጂስት ይህን መገምገም እንዴት ተሳናቸው? ምን ዓይነት ችግሮች ነበሩ እንዴትስ ተፈቱ? በወቅቱ ከሁለቱም ወገኖች የወጡ መግለጫዎች ምን ነበሩ? የችግሩ ምንጭ ምንድነው ብሎ ማጤን ጤናማ ነው። የመኢአድና የኢዴፓ የበርካታ ደጋፊ መኖር ግን ስትራቴጅስቲው እንዳሉት ግምት ሳይሆን እውነት ነው።

የተቃዋሚዎች ተከፋፍሎ ወደ ምርጫ መግባት አስዛኝነትን የተረዱ ወገኖች ራሳቸውን ቀስተደመና በሚል ድርጅት ዙሪያ አሰባስበው “ ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር ለምርጫ ሲባል ኅብረትን ለመፍጠር የተንቀሳቀሱት፤”ም ተብሉአል። ይህ ግዙፍ መሰረታዊ ስህተት ያረፈበት የድምዳሜ መነሻ ነው። ምናልባትም ይሁነኝ ተብሎ ደጋፊ ላማባበል ፤ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ፋይዳ ወይም የሚያውቅ ተከራካሪ የለም ከሚል ስንኩል እሳቤ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ በዚህ ጹሁፍ ብቻ ሳይሆን ከላይ በተመለከቱት ሁለት መጽሃፍት ላይም እንዲሁ ሊነገረን ተወጥኑአል። የታሪክ ሽሚያውም ይሁን መዋሸቱ ሊቆም ይገባዋል።

‘የአንጸባራቂው ገድልና ድል ባለቤት’ ቀስተ ዳመና እንዴት ተመሰረተ? አንዳርጋቸው በወቅቱ ከምስረታው በፊት በኅቡዕ ካልነበሩ በቀር እንደሌሉበት ነግረውናልና ጠይቀውም ቢሆን የተዛባውን እውነታ ቢያርሙት ጥሩ ነው። እንዲህ መሰል ሁኔታዎች ተደጋግመው ሲከሰቱም ነው ፀሃፊውን ከጹሁፉ ወይም ከአቀረበው አመክኖ ለይቶ ማየት የሚከብደው። በመኢአድና በኢዴፓ መሃል የተፈጠረው አለመግባባት ሊረግብ አለመቻል (በሽምጋይነት የቆሙት ያደረጉት አስተዋጸኦ ታክሎበት)ወደ ሌላ መፍትሄ ተሸጋገረ። ሽምጋዮቹ (በአብዛኛው የቀስተ ዳመና መስራች አባላት ነበሩ) ለሃገሪቱ ፖለቲካዊ ሂደት

መለወጥ ከቀማችሁ ለምን በቀጥታ በሂደቱ አትሳተፉም ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምን መልስ ነበር የሰጡት?

ዞሮ ዞሮ ግን በየፓርቲዎቹ ገብተው ልዩነቱን ለማጥበብ ከመሞከር ይልቅ እንደ አንድ ፓርቲ ሆኖ መምጣት የሚለው ሃሳብ ይሁንታን አገኘ ። ቀስተደመና ሃገር አቀፍ ፓርቲ ሆኖ ተመሰረተ። ለፓርቲው የድጋፍ ፊርማ ከመላው የሃገሪቱ ክፍል እንዴት በአጭር ጊዜ ሊያሰባስብ ቻለ? የሚለው የዚህ ጹሁፍ ግብ አይደለምና እንለፈው። ሳንግባባ አልቀረነምና። ነገር ግን ዛሬ ለአዲሱ ፓርቲ የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ እንዲህ ጭንቅ የሆነው ሙሁራኑ በቴሌቪዥን ስላልቀሰቀሱ ይሆን? ጥቂት ጉዳዮችን ልጨምር፤ በዚያ ውጥረት ሰሞን በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪ የቅንጅት አባል ለመሆን እያለ ቅንጅቱ አዲስ ተከራይቶት ወደ ነበረው ጽ/ቤት ይመጣ ነበር። በወቅቱም እዚያ በጋራ ጽ/ቤት ተከራይቶ በነበረው ቀስተደመና ራስቸው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ጨምሮ ይደረግ የነበረው የቀስተ ዳመናን ፓርቲ የአባልነት ቅጽ የማስሞላት ጥድፊያ ጊዜው እንዳለፈበት ተውኔት ቀጥረነው ብናልፈውም ትዝብትን ጥሎ አልፉአል። ይህም ይሁን በተለይም የመኢአድን ወጣቶች በዚያ ሰለ ቅንጅት በሚወራበት ጊዜ ማታ ማታ እየተጠሩ በቀስተዳመና ጽ/ቤት (ስም መጥራቱ ይቅርና) ምን ይባሉ እንደነበርም ማንሳቱ ሌላው እውነታ ነው። ይህም ይቅር ራሱን የቻለ “ጎህ ሲቀድ ይወጣዋልና”።

እነዚህን የሁአላ ታሪኮች ይታወሱ ዘንድ ግድ ያለው ከላይ በተጠቀሰው ጹሁፍ “ለምርጫ ሲባል” የሚል ሃረግና አሁን በተለይም በውጭ ሃገር የሚታየው ሩጫ ነው ። ከመነሻው አቁአራጭ መንገድ የመሻት ህልም መኖሩን እንጂ ረጅሙን ጉዞ የመቀላቀል ቁርጠኝነት እንዳልነበረ ያሳያል። ለዚህም ነው ቶሎ ብሎ የሰላሙ ትግል ተሙአጡአል ፤ ወደትጥቁ ትግል የምንባለው። ነገ ደግሞ እንዲሁ እሱም በአጭር ግምገማ አጭር ይቀራል ማለት ነቢይነት አይደለም።

“ሁኔታው ያስዘናቸው የቀሰተ ደመና  መስራቾች” ኢዴሊን ይዘው ቅንጅትን መሰረቱ ተባልን ። በጣም ያስገርማል። ዛሬ የኢዴሊ ጥቂት ግለሰቦች ከዚህኛው የስትራቴጂስቱ ፊና ሰለቀሙ እንጂ ምን ሊባሉ እንደሚችሉ ሳስበው ይዘገንነኛል። ይሄንንም እንለፈው። እነዚህ ፀሃፊዎች እንዲህ የሚሙአገቱላቸው “ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ” ምን አይነት የትግል እንቅስቃሴ አይተው የድርጅቶቹን ትግል ሊያግዙና ሊያስታርቁ እንደመጡ ቢጠቅሱ ኖሮ አሁንም ከተዛባ ድምዳሜ ባዳናቸው ነበር። ብዙ አስረጂ መጥቀስ ይቻላል።

“በምርጫው ማስገምገም ጅማሮ የነበረው የአብዛኛው ሕዝብ እይታ የጨለምተኛነት ነበር” ተብሉአል። እንዲህ አይነት ጥቅል ድምዳሜዎች ናቸው ስህተት የሚሆኑት። በምን አይነት ጥናት እንደተረጋገጠ ባናውቅም ጨለምተኛ አስተሳሰብ ይዞ ነበር ሲሞት፤ ሲታሰር፤ ሲታገል የቆየው ብሎ ለመቀበል ይቸግራል። ወይስ መሪዎቹን ከአውሮፓና ከአሜሪካ ማስመጣት ነበረበት ለማለት ይሆን? ወይስ ዛሬም ለዚያ ሕዝብ ያለው ዝቅ ያለ የወያነ ግምት በአንዳንዶቻችሁ ውስጥ ተጣብቶ ቅርቱአል? ይሁንና ግን ይህ ለምን እንደተባለ ትንሽ ወረድ ብሎ ሰለምናገኘው መረዳት አያዳግተንም። “በቅንጅትና በህብረቱ ውስጥ የተሰባሰቡት የሃገሪቱ ታላላቅ ምሁራን በቴሌቪዥን እየቀረቡ . . . ያደረጉት ቅስቀሳ የሕዝቡን እይታ እየለወጠ ሄደ . . . ይህ የተለወጠ እይታ . . . ሕዝቡ ለምሁራን ከሰጠው አመኔታ ነበር።” አዎ! ምሁራኑ ድርሻ እንዳላቸው አንካካድም። ትናንሾቹ ነፋሳት ከስማቸው በፊት ማዕረግ ባይኖር ሥራቸውና ድካማቸው ይታወስ ማለትና የተዛባው ድምዳሜ እንዲታረም ግድ

ይላል እንጂ። ይህ ተደጋግሞ ታይቱአልና። እነርሱ እኮ የግድ ስቴት ዲፓርትመንት መጥተው ስለእስረኛ አሃዝ መመስከር አይጠበቅባቸውም ወይም ስፖንሰር ፈልገው ጥናት ማጥናት አይኖርባቸውም።

ሌላም አለ። “በምርጫ የቅስቀሳ ወቅት ወያኔ በሰላም ከሥልጣን እሺ ብሎ ስለመውረዱ በወሎ አርሶአደሮች ለሙሁራኑ ላቀረቡላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ … እናንተ ምረጡንና እናሸንፍ፤ አልወርድም ቢል ጌቶቹ (አሜሪካኖች ) አይለቁትም” የሚል ነው ብለዋል። እዚህ ስብሰባ ላይ አንዳርጋቸው መገኘታቸውን እርግጠኛ አይደለሁም። (ሌላውን ፀሃፊ ባላውቃቸውም) ሙሁሩ ግን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እንደሆኑ ለምን መግልጽ እንዳልፈለጉ አላውቅም። አስታውሳለሁ ያሬድ ጥበቡም ነበሩ። ይህ ሁሉ ድርድር ለምን እንደሆነና የሚሰበከው የኃይል አሰላለፍና የፊና ሩጫ ምን እንደሆነ ሁሉም ሊረዳ ይችላል። ለምን ሳውላ ፤ አፋር ፤ ቤንሻንጉል ፤ ጅማ ፤ ደ/ታቦር ፤ ደባርቅ ፤ የቦቅላ ፤ ደጀን ፤ ጅማ ፤ አሰላ ፤ ሶዶ ፤ አርባምንጭ ፤ ወልዲያ ፤ወዘተ ከተካሄዱት ሊጠቀስ አልተፈለገም? ሰላማያውቁት ወይስ ሙሁራኑ ስላልተገኙ? ወይስ ሌላ? ይችን የምትመር ኅምዛዛ እውነት መቀበል ግድ ነው። አድመኝነት ፤ የፊና ሩጫ ፤ ብልጣ ብልጥ ጮሌነትም ይሁን ስትራቴጂስት መሆን እውነትን ሲጋፈጡ ነው።

ይህን መሰሉ አነጋገርም ነውር ተደርጎ ቢታይ አልደነቅም። ዳሩ ይህን ሁሉ ዋጋ የተከፈለበትን የሰላማዊ ትግል እሴት “ሠላማዊ ትግል በተባለ ርዕዮት ቀመስ ትብትብ የታነቀ” የሚልን ባለጊዜ ለመናገር ሌላ አቻ ቃላትን መጠቀም በተገባ ነበር። በእኔም ይሁን በሌሎች ኢትዮጵያውያን ዘንድ ቅንጅትም ይሁን በወቅቱ የተሰለፉ የተቃውሞ ሃይላት ድጋፍ ሊያገኙ የበቁት የሰላሙን ትግል አብርትተው በመያዛቸው ፤ ይህም ዘላቂ ሰላምንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ሊያስገኝ እንደሚችል ማስተማርና ማሳመን በመቻላቸው ነው። ይህን የህዝብ እምነትና ግንዛቤ እንደ ቂላቂልነትና አይረቤ ጉዳይ መቁጠር ባይከለከልም ትክክል ነው ማለት ግን አይደለም። ምናልባት ይህን መንገድ በብርቱ መሞገት ከሚፈለገው የድምዳሜ ጠገግ እንዳያስወጣ በመፍራት ሊሆንም እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

አሁንም አገላለጽ ከዚህ ጹሁፍ ልዋስና ይህንን የትጥቅ ትግል ጥሪ አቀራረብ ርዕዮት ቀመስ የትጥቅ ትግል ትብትብ ብንለው “እንደ ተለምዶ መድብል ” እንደሚቀጠር እርግጠኛ መሆን ይቻላል። ይህን ካልን ዘንድ ከዚሁ የትጥቅ ትግል ትብትብ ከቀርቡ ሃሳቦች ላይ አንዳንዱን እየጠቀስን ተንሽ እንወያይ እስኪ።

“መለስ ዜናዊ በሩቁ ማሰብ የማይችል የዕለቱን ብቻ ለመወጣት ሲያሰላ የሚውልና የሚያደር ትልቅ ታከቲሺያን ነው።” ተብሉአል። መቼም በየመሃሉ እየሄዱ የሚሰነቀሩ ሃረጎችን እንደኔ ብጤው አላዋቂ እንዲሁ እንደገቡ ይቆጥር ይሆናል። ለአብነትም ይህ የተሰመረበትን አይነት። የአቶ መለስ ትልቅ ታከቲሺያንነትም ሊነገረን መሆኑ ነው። ለብዙዎቻችን ይህን የመሰለ አረመኔአዊነትና ገዳይነት እንዴት ታከቲሺያን ሊያሰኝ እንደቻለ አናውቅም። ምናልባት የአንድ የሰም ድረ ገጽ ባለቤት ይህን ቅጽል ለአንዳርጋቸው ሲሰጥ የኖረው ከዚህ ተውሶ ይሆን? አላውቅም።

ሰላማዊ ትግሉን ለማንኳሰስ ሲባል ሌላው በቅንጅቱ ላይ የቀረበው ወቀሳ ድምጹን ለማስከበር ዋናው መተማመኛ ከሕዝብ ጋር መተሳሰር ነበረበት የሚል ነው። ግራ የሚገባ አባባል ነው። አሁን ፊና አበጅቶ በዲያስፓራው ከሚተራመሰው ጋር ለማለት ካለሆነ በቀር (እድሜ ለናንተ) ቅንጅቱም ሆነ ኅብረቱ እስከምናውቀው ድረስ ዋንኛ መተማመኛቸው ህዝቡ ነው። ያለመታደል ሆኖ ጥቂቶች አሳልፈው

ሰጡት፤ በሞቱ ደነከሩበት። ዞሮ ዞሮ ይህ ምስጢር ባይሆንም ለ"ትብትቡ" ደምዳሜ አንቅፋት ይሆናል በሚልና እንዲሁ በጭፍን የድጋፍ ፊና የሚሮጡትን ለማባበል እንደተደረገ ጥረት አይተነው ይህንንም ልናልፈው እንችላለን። ተከትሎ የቀረበው ገለጻም ይህንኑ ያረጋግጣል።"ሕዝብ ለተቀነባበረ ሕዝባዊ ትግል በየራሱ ተነሳሽነት ሊዘጋጅ የሚችልበት ዕድል ይፈጠር ነበር" ይላል። ይህም ከላይ ለቀረበው ርዕዮት ቀመስ ለሆነው የትጥቅ ትግል ትብትብ ደጋፊ አመክንዮ መሆኑ ነው።

ትላንት እነፕ/ር ዓሥራት ፤ አሰፋ ማሩ ፤ … ሲታሰሩና ሲገደሉ ሙሁራን መሪዎቻችን ምን ስትሉና ምን ስታደርጉ እንደነበር አለመናገር እኮ አላዋቂነት አይደለም። ለሁላችን የምትሆን ሃገር ለመመስረት ከሚናፍቅ ዜጋ የሚጠበቅ ምግባር እንጂ። በተቃዋሚዎ ድርጅቶችም ይሁን በሕዝብ ላይ ዝቅ ያለ ግምትን አሳድሮ መነሳት ተገቢ አይደለም። አሁንም ለዚህ አገላለጽ አብነት ለመጥቀስ እወዳለሁ።

" ተቃዋሚዎች ለሕዝቡ የሰጡት ሚና ተኛ ሲሉት የሚተኛ ፤ ተነስ ሲሉት የሚነሳ " ተብሎአል። ይህ የጸሃፊዎቹ የዕይታ አድማስና ድምዳሜ ነው። እንዲህ አይነት ሃሳብ በምናቀርብበት ወቅት ራስን በዚያ ቦታ አድርጎ መመልከት ጥሩ ነው። በርግጥ ፀሃፊዎቹ እንዲህ አይነት ተኛ ሲባል የሚጋደም ፤ተነስ ሲባል የሚነሳ ስብዕና ይኖራቸው ከሆነ ወይም እነሱ ሲያደራጁት ብቻ ሕዝቡ ይህን መሰል ስብዕና አይታይበት ከሆነ አናውቅም።ሁላችንም የምንረዳው ግን ተጎንባሽ የተባለው ሕዝብ ሥልጣን በእጁ መሆኑን እንዲያረጋግጥ ፤ የሚመራውን እንዲመርጥና እምቢኝ እንዲል ነው እንዲያውቅ የተደረገው ። ለዚህም ነው ከመሬቱ ሲነቅሉት ፤ ጣሪያውን አውልቀው ሲወስዱበት ፤ ሲገርፉትና ሲያሰቃዩት ፤ ሲገድሉት እምቢኝ ወዘተ ብሎ ከትግሉ ያላፈገፈገው። ተኛ ሲባል የሚተኛ ቢሆንማ ኖሮ ሌላው ቢቀር እንዲያ በነቂስ ውጥቶ ባልመረጠ ነበር። እንዲህም ሲባል ግን በጹሁፉ የተመለከተው ገለጻ ይሁነኝ ተብሎ የተመረጠ "ትብትብ" መሆኑ ግልጽ ነው። ምናልባትም ለአዲሱ የትግል ስልት እንዲያ አይነት ሰው ተፈልጎ ከሆነ ይቅናችሁ ፤ ከአሁኑ አንዳንድ ፍንጭ ከፓልቶክ ሃይላችሁ በኩል እንደምታገኙ እየታየ ነው።

እንግዲህ በዚህ ፊና የቀማችሁት የቱንም ዓይነት ተነሳሽነት ወይም ፍላጎት ይኑራችሁ በሰላማዊ ትግል ላይ ትዕግስታችሁ ማለቁ ብቻ ሳይሆን ጥላቻ አሳድራችሁአል።ሌላ ጭስ አልባ ኢንደስትሪ የማቁአቁአም ህልም ስላላችሁ ነው ብዬም እንደአንዳንዶች አልገምትም። የጥላቻ ገለጻው ግን በጹሁፉ ተካቱአል። እንዲህ ይነበባል፤ "ከሰላማዊ ትግል ጋር ሙጭጭ ማለት ግን ከየት እንደሚመጣ መናገር አስቸጋሪ ነው" ይላል። ይህ በቀጥታ ከጹሁፉ የተወሰደ ነው። ከትጥቅ ትግል ጋር ሙጭጭ ማለትንስ ቅድስና ነው ያለው ማነው? ቢባል መልስ ልትሰጡ እንደምትሞከሩትና የናንተን ባላ ሌላው እንዲያከብርላችሁ የምትሹትን ያህል ለሌላውም ይሂው ከናንተ ይጠበቅ ነበር። የኔ ብቻ ልክ ፤ ተቀበሉኝ ፤ አታደናቅፉኝ ወዘተ የሌላውን እያበሻቀጡ ለዚያውም ከሙሁራን መሆኑ ማሳዘን ብቻ ሳይሆን በጣም ያሳፍራል።

ራሳችሁን ' ከጀግኖቹ' ተርታ በማቀም የትጥቅ ትግሉን ከመፍራት ነው? የሰላም ትግሉን ሙጭጭ ያሉት በማለት የሰላማዊ ትግል ተቿዦችን ጽናታቸውን ለማጠየቅ ሲባል እንዲህም ተብሉአል። የሞራል ተጠያቂነቱን ጉዳይ አያስፈልግምና ሾላ በድፍን እንለፈው ። ካስፈለገ ሌላ ጊዜ መመለስ ችግር አይደለምና። ለነገሩ ሰላማዊ ትግል መግደል ወይም ማስገደል ሳይሆን ሞትን በድፍረት መጋፈጥን የሚጠይቅ ወኔ ያለበት የደፋሮች ትግል ነው። በዚህ እንከራከርምና አንድ ተጨማሪ ነጥብ ጠቅሼ ይህን

ጉዳይ ላብቃ። “ ስለ ሰላማዊና ህጋዊ ትግል በዚያን ወቅት ይለፈፍ የነበረው ፤ ሰበካው ሌላ የትግል ስልት እስኪቀረጽ ድረስ ለጊዜ መግዢያነት የሚያገለግል ታክቲክ ቢሆን ብቻ ነበር ። ሌላው ሁሉ ቀልድ ነው። ”የሚልም ሰፍሮ እናገኛለን።

እዚህ ላይ ፍላጎቱ ሁሉ ይፋ ወጣ። ምናልባትም ባላችሁበትና ዜግነታችሁ በተከበረበት ሃገር ላይ ቆሞ ይህን መናገርም ሆነ በሌላው ቁስል እንጨት መስደድ ከባድ አይደለም። የሚያሳዝነው ይህ ጉዳይ በወቀሳ መልክ ለዚያውም ራሱን ትልቅ ስትራቴጂስት ካደረገ ሰው ሲወጣ ነው። ይሁንና ግን የዚህ ሁሉ ማሰሪያ ለቀረበው የትጥቅ ትግል ትብትብ ደጋፊ ይሆናል በሚል ቂላቂል ሂሳብ ነውና እንለፈው ። ከዚህ የምንረዳው የራስን መንገድ ለማስከበር የሌላውን ማክበር እንደሚያሻ ነው።

ወደ ተከታዩ ጉዳይ ስንሸጋገር ደግሞ ልሂቃኑ በሰላማዊ ትግል ላይ ያቀረባችሁት መከራከሪያ ዥው ብሎ ይወርዳል። ሠላማዊ ትግል “የህግ የበላይነት መስፈንን እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚጠይቅ ነው” ይላል። ይህ አባባል አንድ ሰውን አስታወሰኝ፤ በአስከስታ ወራጅነቱ የማውቀውንና አሁን የዚህ ወገን “የፕሮፓጋንዳ ሚኒስትር ” የሆነው አበበ በለውን። በሚያቀርበው የሬዲዮ ስርጭቱ (መቼም ጋዜጠኝነት ባለቤት የሌለው ክፍት ደጃፍ ሆኑአል) ያጠናው “የህግ የበላይነት” የምትለዋን ነው መሰል እንዲሁ ጀምሮ እስኪጨርስ ሲለው ይውላል። ወደ ጉዳዬ ልመለስ። እስከሚገባኝ ጊዜ ድረስ ሠላማዊ ትግል ግቡ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ነው፤ ይህ ከተረጋገጠ እኮ ትግል አይስፈልገንም ። በተረጋገጠው ህግ ተመርኩዞ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች አማራጮቻቸውን ለሕዝቡ እያቀረቡ የሚወዳደሩበት ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው። ዛሬ የሁሉም ጥያቄ የህግ የበላይነት ይረጋገጥ ነው። ማለትም ሁሉም ለህግ ይገዛ ማለት ይሆናል። ከተሳሳትኩ ለመታረም ዝግጁ ነኝ።

ይህ እውነታ በጸሃፊው ዘንድ ይዘንጋል የሚል የዋህ ግምትም የሚያድርበት ላይኖር ይችላል። ሆነ ተብሎ ዙሪያውን በተሰበሰቡ በመልክ ቀርቶ በስም የማይተዋወቁትን የፓልቶክ ታንቲረኞችንና ግፋ ቢል የዕቅዱ ስፖንሰሮችን ግራ ለማጋባትና ለማስደሰት ይሆናል። እንደሚሰማው ከሆነ ሳይሳካ የቀረ አይመስለኝም ። አንዳንዶቹማ “የተራበውን መንፈሳችን ጠጋኝ ፤ ስትራቴጂስታችን” እያሉ መጋበዝ ጀምረዋል። ገፋ አድርገውም የደረሰ እህል ላማጨድ ደቦ እንደተጠራ የአገሬ ልጅ “ ዱብ ዱብ እያልን አመራር እንጠብቅ ” ያሉም አሉና እንደ አገራችን አይዶል ሾው ዳኞች ”ለዛሬው ተሳክቱአል” ልል ፈለኩ።

“አመፅ የራሱ ዳይናሚክስ አለው” ተብሉአልና “ዳይናሚክሱን” ለማየት እድሜ ይስጠን። በተጨማሪም በዚህ የትጥቅ ተግል “ትብትብ” እንደተባለው ሠላማዊ ትግል ሥልጣን ላይ ያለውን ጨቁአኝ በመለመን ፤ በመማለድ ፤ የጠየቀውን በመስጠት ፤ ሲጋፋ መንገድ በመልቀቅ የሚከናወን አይደለም።ሌላም ላክልበት ። የኢትዮጲያ ችግር የግድ ተራራ ላይ ቁጭ ብለው ስላጠኑት ወይም ከተራራ ጫፍ ስለተኮሱም አይፈታም። የተጀመረው የእምቢታ ትግል ተጠናክሮ ሲቀጥል እንጂ። ወያነም የማያውቀው መንገድ ነውና።

የዴሞክራሲ ጥያቄ የቱንም ያህል ብንመኘው በአንድ ጀንበር የሚከሰት ለውጥ አይደለም። ሂደቱ ያልተቁአረጠ እንዲሆን እስካስቻልነው ድረስ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ይኳለብታል። በትውልድ ውስጥ እያደገ የሚሄድ ሲሆን ዘለቄታውም የዚያኑ ያህል አስተማማኝ ይሆናል። በሰላማዊ

መንገድ የሚታገሉትን ፈሪዎች፤ ተኩላሾችን ጀግኖች የሚለው የፖለቲካ “ትብትብ ” አስተሳሰብ አሉታውም ከዚህ ይመነጫል።

የሠላማዊ ትግሉን ተሞክሮ የማጠናከሪያ አፍታ እንዳይኖር በአንድ በኩል አገዛዙ በሌላው የስም ተቃዋሚዎች በመንገዱ መጋረጥ ጊዜውን ቢያረዝመው ከማዘንና ወደፊት ለመራመድ ከመሞከር ውጪ ምንም ማድረግ አይቻልም። የማይሞቁትን እሳት እያነደዱ ዞር ማለት ሊያበቃም ግድ ነው። የቅንጅት መሪዎች እስር ቤት እያሉ “ዓለም አቀፍ አመራር” በሚለው ትብትብ ተዘጋጅቶ ወደ ሃገር ውስጥ የገባው የቀን መቁጠሪያ ካላንደር በናንተ እይታ የሰላማዊ ትግል ጥሪም መሆኑ አይደለ? አሜሪካ ሆናችሁ የጠራችሁት የአድማ ጥሪ ገቢር ባለመሆኑም የሰላም መንገድ ትዕግስታችሁ ተሙአጠጠ። በዚያ የቀን መቁጠሪያ የመጣውን መዘዝ እንተወው። የሰላም ትግሉ እንደ ጊዜ መግዣ ቢሆን ጥሩ ነበር ሲባል፤ ለዚያውም ዛሬ ላይ ተቁሞ የሚገርም ነው ። ይህ ጨዋታ በዲያስፖራው መሃል ለመነገድ ካልሆነ ሌላ ሊሆን አይይችልም። አንድ ነገር በርግጠኝነት ላንሳ። አዲስ አበባ ውስጥ አሁን አንድ የተቃውሞ ሰልፍ ቢጠራ በዚህ ዙሪያ ጀብ ጀብ የሚሉት ናቸው በቀጥታ ለቤተሰቦቻቸው እየደወሉ እንዳትወጡ፤ ይፈጁአችሁአል የሚሉት። ፍርድ እንደራስ ቢሆን ጥሩ ነው።

በቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ዘመን በጥናትና ምርምር ፤ በድርጅታዊ ሥራ ስም የመዋጮ ገንዘብ ያነወሩ ዛሬ ሌላውን ሊንቅፉ ሲነሱ ያሳዝናል። ይሄም ቦታ አለውና ልተወው። ነገር ግን እንዲህ አይነት ኃይል ከሁአላው ቆሞ በምንስ መንገድ ህይወትን ያህል ውድ ዋጋ ለመክፈል ለሚያስችል ተግባር አብሮ መሰለፍ ይቻላል? ወይስ ሆቴልና አውቶቡስ በማፈንዳት በሚፈስ ደም ለሚገኝ የፖለቲካ ትርፍ ሩጫ ? ወይስ በአንድ ወቅት የእኛን አማራጭ ካልተቀበላችሁ ቅንጀትን ለቃችሁ ውጡ የተባለው ቁጣ ይመጣ ይሆን? በአዲሱ ድርጅታዊ ምልመላ የተካተቱትም ጉዳይ የዚህ ርዕሰ ጉዳይ ክፍል አይደለምና አናነሳውም። ነገር ግን በጥላቻና በቡድን ስሜት፤ በተዛባ ግንዛቤ የታጀለ የትግል “ትብትብ” የትም አይደርስም። ዛሬ አስተዋጾአቸውን ማክበር ቀርቶ ስማቸውን ለማንሳት አንዳንዶቻችሁ የሚተናነቃችሁ የሰላሙ ትግል አርበኞች በእርግጠኝነት መንገዳቸውን ቀጥለዋል።

ሁላችንም በአንድ ጉዳይ ልንግባባ እንችላለን ፤ ሌላውን ሁሉ ትተን። ከላይ እስከ ታች የነቀዘው የወያነ ሥርዓት ለሃገሪቱ ደህንነትና ህልውና ሥጋት ነው። ይህም ሲባል በሃሰትና በታየ ኢ-ተአማኒ ድርጊት ለአጉአጉል ብልጣ ብልጥ የፖለቲካ ትብታቦች መሰዊያ ላይ የምናገደም በግ አንሆንም።

ዛሬ ምናልባት ለአንዳንዶቻችሁ የስዬ አብርሃና የወንድሞቻቸው መታሰር ለአገዛዙ አረመኔአዊነት መገለጫ ሊሆን ይችል ይሆናል። እነስዬ አብርሃ ከተፈቱም በሁአላ የሚያሰሙት የተሸናፊነትና የተገዢነት የሥነ ልቦና ወረራም ልባችሁን አማልሎት ይሆናልም። በምድረ አሜሪካ ከደጋፊዎቻችሁ ጋር ያደረጋችሁት አጀብም ይሄንኑ ቢያሳይ አይፈረድም። የዛሬው ሰለባ ስዬን ደግሞ የምንጠይቃቸው ብዙ ነገር አለ። ብዙ ብዙ ዓሥራቶችን ነጥቀውናል እኮ። ከታሰሩትና ከተገደሉት ሌላ እስኪ ስለታፈኑት እኒያ ወገኖቻችን ጠይቁልን ። ከዚህ የሚዛን ነጥብ ስንነሳ ዛሬ አጋር መሆናችሁ ተጨፍኖ ሊከተላችሁ ለቆመው እንጂ ለብዙዎችማ ሚስጢር አይደለም። ትስስራችሁ የጠና ነውና። ይህ ንጹሃን የሞቱበትን ትግል ተርካችሁ ያወጣችሁትን “ግለ ታሪክ” እንኩአ መታሰቢያነቱን ልትሰጡ የደፈራችሁት ለነርሳቸውስ አይደለ? መብታችሁን ለመጋፋት እንዳልሆነ ይታወቅልኝ።

እንግዲህ አዲሱ የትግል ስልት “ትብትብ” በሃገር ውስጥ በጎቡዕ ፤ በውጭ ደግሞ በግልጽ አሰራር የተዋቀረ መዋቅር እንደሚኖረው ታውጇል። ድንቅ ዕቅድ ። በርግጥም አዛዥ ጄኔራሎችም ከፓልቶክ ጉአዳም ይሁን በጡረታ ካሉትም ፈላልጎ መሙላት ነው። ወያነ (በዚህ እቅድ ውስጥ ከሌለ) እንደው ቂላቂል ሞኝ ነው ፤ ቁጭ ብሎ የስትራቴጂስቶቹን የተራራና የፓልቶክ ጥናት ውጤት ይጠብቃል; “. . . እንቶኔ በጌታው እንቶኔ ይፎከራል” አሉ።

ሕዝብ የስልጣን ባለቤትነቱን እንዲያረጋግጥ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ከሃይል አዙሪት የሚወጣበት ዘመን እንዲመጣ የየበኩላችንን ጥረትና ድካም ይጠይቃል።በሚቀጥለው ጹሁፎቻችን እንደምንገናኝ ተስፋ አለኝ። ስለመትረየስ ዋጋ በፓልቶክ ሲወራ እንደሰማሁት ውድ እንደማይሆን ተስፋዬም ነው። አበቃሁ።

ሳሚ ሊ